EthioLion

# የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን መደበኛ አመታዊ ጉባኤውን አካሄደ!!

የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን መደበኛ አመታዊ ጉባኤውን በርካታ ሴቶችና ወጣቶች በተገኙበት በነሐሴ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ አካሄደ። ይህ ከተለያዩ ቅርንጫፍ ማህበራቱ የተገኙት አባላት ጉባዔያቸውን የጀመሩት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት፣ ፍትሕና እኩልነት ለተሰው ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች የሕሊና ጸሎት በማድረግ ነበር። ከህሊና ጸሎቱ ቀጥሎ የኮሚቴው አመታዊ የሥራ ዘገባ በሊቀመንበሩ አቶ ሰለሞን ገብረመስቀል በዝርዝር ቀርቦ ውይይት ከተካሄደ በኋላ፣ በድርጅቱ ስር ተደራጅተው ያሉ ቅርንጫፍ ኮሚቴዎችም የበኩላቸውን ዘገባ ለቤቱ አቅርበዋል። በቀረቡት ዘገባዎች ላይም ውይይቶች ተካሂደዋል።

ከዚያም የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር ዘነበ ተሾመ በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በሥሩ በርካታ ሴቶችንና ወጣቶችን በአባልነት አቅፎ መንቀሳቀሱን አስመልክቶ ያላቸውን ከፍተኛ አድናቆት በመግለጽ ኢሕአፓን የመሰረቱና በተማሪው በተለይም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የትግል እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና ይጫወቱ የነበሩት ከ45 አመታት በፊት ለሴቶች ጥያቄ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሴቶች በራሳቸው ለብቻቸው እንዲደራጁ ያደረጉት ጥረት ፍሬ አግኝቶ በኢሕአፓም ሆነ ከሱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ከነበራቸው እንደ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች፤ ሰራተኞች፣ ወጣት ሴቶች፣ በጦር ትግሉም ጭምር በርካታ የጀግንነት ታሪክ ሰርተው ማለፋቸውን ገልፀው በበለጠ ወ/ሮ ገነት ይበልጥ ሊያብራሩ እንደሚችሉ ጠቅሰዋል። ይህ የወደፊቷን ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆነው አዲሱ ትውልድም የራሱን የትግል አሻራ በሀገሪቱ ታሪክ ላይ እንዲያሳርፍ የዚያን ትውልድ አርአያነት እንዲከተሉ ወገናዊ ጥሪ አቅርበዋል። በዚህ በኩል ኢሕአፓ ማንኛውንም ድጋፍና ትብብር ለማድረግ ምንጊዜም ዝግጁ እንደሆነም ገልፀዋል።

በማስከተልም በአዳራሹ የተሰቀሉትን ሥዕላዊ የታሪክ ሂደቶችን መሰረት በማድረግ በዛሬው እለት ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 38 ኛ አመት በዛሬው ዕለት ከተሰብሳቢው ጋር ለምን ማስታወስ እንደሚያሻ አፅንዖት የሰጡበትም ነበር። ይኸውም

1. ኢሕአፓን የመሰረቱት በአፍላ ዘመናቸው የነበሩ ለሀገራቸውን ለሕዝባቸው ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸው፤ የሕዝባቸው በድህነትና በመብት አልባነት መኖር ያንገበገባቸው ወጣት መሆናቸው፣
2. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው አንጋፋ ፓርቲ ከመሆኑ ሌላ ላለፉት የትግል አመታት ባደረጋቸው እልህ አስጨራሽ ትግሎች ለወጣቱ ትውልድ በአርአያነትና በምሳሌነት የሚታይ በመሆናቸው፣
3. ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ይኸው ላለፉት 38 አመት በጽናት ትግላቸውን ቀጥለው ድርጅታቸውንም ከማኝናውም ጥቃት ተከላክለው ከተሰብሳቢው ጋር በዛሬው ቀን ለመገናኘትና ለመወያየት መቻላቸው፣

EthioLion

4. አንግበው የታገሉላቸውና ከፍተኛ መስዋዕት የከፈሉባቸው ጥያቄዎች ምንም እንኳ ሕዝባችን የሥልጣን ባለቤትነቱን በሚገባ ለመጨበጥ ባይችልም በርካታ ድሎችን ማስመዝገባቸው፣
5. በተለያዩ የባዕዳን ወረራ ጊዜ ሕዝባችንን የሚያኮራ ታሪክ የሰሩትን ዜጎቻችን በማስታወስ እንደምናከበር ሁሉ በኢሕአፓና በሌሎችም ሀገር ወዳድ ሃይሎች የተሰሩትን የጀግንነት ታሪክ አብሮ ማስታወሱ ለወደፊቱ እንቅስቃሴያችን ወሳኝነት ያለው መሆኑን በሰፋት ገልፀዋል።

በመቀጠልም የፖለቲካ ስደተኝነት ጥያቄያቸው ተሟልቶ የተረጋጋ ኑሮ ለመጀመር እድሉን ላገኙት የደጋፊ ኮሚቴው አባላት የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈው ኢሕአፓ ለነጻነትና ለመብት መከበር ለሚያደርገው ትግል ያደረጉትን ድጋፍ ወደፊትም እንዲቀጥሉበት አጽንዖት ሰጥተው አደራቸውን አስተላልፈዋል። የዚህ አይነት እድል ለማግኘት ለሚጠባበቁትም ኢሕአፓ ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ ወደፊትም የድጋፍ ትብብሩን እንደሚቀጥልበት ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታን አስመልክቶም በዘገባቸው በሰፊው እንዳብራሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሐብ አለንጋ እየተገረፈ ባለበት፣ ሰራ አጥነት በተንሰራፋበት፣ ኤይድስና የወባ በሽታ ሕዝብን በሚጨርሱብት፣ ገበሬው ከመሬቱ እየተፈናቀለ መሬቱ ለህንድና አረብ ከበርቴዎች እየተሸጠ በሚገኝበት፣ በኤሌክትሪክ ሃይል እጦት የተነሳም ፋብሪካዎች ቆመው ሰራተኛውን ለሥራ አጥነት እንዲዳረግ በተደረገበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ11 በመቶ አድጓአል እየተባለ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ውሃ የማይቋጥር ለመሆኑ ግልፅ ከሆነ ውሎ ያደረ እንደሆነም ገልፀዋል። ለዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ የመለስ አገዛዝን ከጫንቃው ላይ ለማውረድ ባለው አቅም ሁሉ እየታገለው ከመገኘቱ ሌላ አሳማኝ ምስክር እንደሌለ አብራርተዋል።

በማያያዝም ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ወጣት ሴቶችን ወደ አረብ አገሮች በመላክ ለሴተኛ አዳሪነትና ለዘመናዊ ባርነት መዳረጉን ቅዱስ አላማው አድርጎ ገፍቶበታል፣ ሕዝቡን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ማበጣበጥና ማጨራረስ የአገዛዙ አቢይ አላማ በማድረግ ግፋ በለው ወደፊት ሲል ይታያል። በመሆኑም ከዚህ ስቃይና መከራ ለመገላገል የሚቻለው ተደራጅቶ በመታገል እየታገሉም ትግሉን ከሌሎች ሀገር ወዳድ ኃይሎች ጋር በማቀነባበር መሆኑንም አፅንዖት ሰጥተው አብራርተዋል። ከዚህ ሁናቴ ለመድረስ ኢሕአፓ በቅርቡ ይፋ ያደረገው የውይይት ጥሪ በጥሞና መታየትና መጠናት ያለበት አቢይ ርዕስ መሆኑንም ገልፀዋል። በመጨረሻም የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን ከተመሰረተ ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ አባላቱ ለኢሕአፓ ላደረጉት የሃሳብና የማቴሪያል ድጋፍ በኢሕአፓ ከፈተኛ አመራር አካል ሥም ምስጋናቸውን በማቅረብ ንግግራቸውን ደምድመዋል::

EthioLion

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ትንታኔ በኋላ ወይዘሮ ገነት ግርማ ሴቶች ራሳቸውን በራሳቸው ነፃነታቸውን ጠብቀው የመደራጀት ጉዳይ አስፈላጊነትን በካናዳና በፈረንሳይ ሀገር በስደት በሚኖሩ ሁለት ኢትዮጵያ ሴቶች ለሞት መዳረጋቸውን በምሳሌነት በመጥቀስ እንደዚህ አይነቱንና ሌሎችንም በኢትዮጵያዊያን ሴቶች ስደተኞች ላይ እየደረሰ ያለውን ችግርና ሰቆቃ ለማስቆም በአንድነት ተቀራርቦ መስራት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል። ዛሬ በመላው ዓለም በተሰደዱ የኢትዮጵያ ሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን መከራ፣ ዘመናዊ ባርነትና የሞት አደጋ መከላከል የሚቻል መሆኑንም በአጽንዖት አብራርተዋል።: በተለያዩ ሀገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በዓለም አቀፍ ኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ሥር በመደራጀት ነጻነትና መብታቸውን ከማስከበር አልፈው ለሌሎች እልፍ አእላፍ እህቶቻቸው ቤዛ ሊሆኑ እንደሚችሉም የድርጅቱን እንቅስቃሴ በምሳሌነት አመላክተዋል።

በእለቱ የደጋፊ ኮሚቴ ስብሳባ ላይ በርካታ ሴቶች የተገኙ ሲሆን፣ በኮሚቴዎች የአመራር ሃላፊነት ቦታዎች ላይ ስፊም ድረሻ እንዳላቸው ተገልጿል። በመጨረሻም የኢትዮጵያን ጊዚያዊ ሁኔታ፣ የሴቶችን ጉዳይ እና የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በተመለከቱ በርካታ ጥያቄዎች ቀርበው ከእንግዶቹ በኩል ሰፋ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው የዕለቱ ትዕይንት ተፈጽሟል።

ነሐሴ 10 ቀን 2002 ዓ.ም.

ፍራንክፈርት / ጀርመን

EthioLion.com